# የወያኔን ጠባይ ቀድመው የተረዱ፤

የወያኔን ጠባይ ቀድመው የተረዱ፤
የቆረጣ ስልቱን ስፋትና ወረዱ፤
በጥቅል በዝርዝር ደጋግመው ያስረዱ፤
መልሰው ራሳቸው እንዴት ተጠመዱ?

መጠኑ ስፋቱ የጎጠኛ አእምሮ፤
እንደ እንቁራሪቷ የራሱ ዓለም ፈጥሮ፤
ግዙፉን ኑባሬ ቆርጦና አሳጥሮ፤
እያተራመሰ ህዝቡን አደናብሮ፤
ለመግዛት ማሰቡን አታሎ አጨናብሮ።

ቀድመው የተረዱ የወያኔን ጠባይ፤
ደጋግመው ያስረዱ ቆመው በአደባባይ፤
እንዴት ተሳናቸው ወያኔያዊው አባይ፤
ሲያጓራ ሲያቅራራ በእውነት አናትላይ።

በረሃብ ጦርነት አገሩን አውኮ፤
ግዛቱን ሲያበዛ በከርሳሞች ምርኮ፤
እራሱ ሰው ገድሎ በሌላው አላኮ፤
መልሶ እንደሚከስ ፈጠራ ተርኮ።

“የወያኔ ወጥመድ ከጥንት የገባቸው፤
ባህርይው መሆኑን እንዴት ተሳናቸው?”

በሐሰት ውንጀላ ሁሉን ይከስና፤
በፍርድ አካሂዱ ሁሉን ያስረሳና፤
በፈጠረው አጀንዳ ቆልፎ ይጠምድና፤
ወንጀሉን ያስረሳል ዳጋግሞ እንደገና።

መረዳት ተስኖት የቆረጣ አካሄድ፤
በፍቱኝ ኑዛዜ ተይዞ ሲጠመድ፤
የቅራኔው ውሉ በብዠታ ሲነጉድ፤
ወያኔው ይስቃል ተቀምጦ ከጉድጓድ።

ታላቁን ጥያቄ ሁሌ እያስረሳ፤
ትልቁን እየተወ ትንሹን እያነሳ፤
ተቃዋሚን ሁሉ እያሳየ አበሳ፤
ወያኔው ያስካካል ስነጉድ በዳበሳ።

እኔን ያሳዘነኝ ብዙ ያነበቡ፤
በልፈታ አባዜ ሁልጊዜ ሲያነቡ፤

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለቆሙለት ቀርቶ ስለራስ ሲያስቡ፤
በአካሄድ ሲረሳ የደም ማህረቡ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com